# ያን ያህል ወጥ መርገጥ ምን የሚሉት ድፍረት ነው?

በእውነቱ ዘለቀ

*Tigrai Online December 18, 2016*

**Gedu Andargachew: A fifth column on the loose** (5ኛ ረድፈኛ የሆነው ገዱ አንዳርጋቸው እንዳሻው ሲፏልል) በሚል ርዕስ ብርሀነ ካህሳይ የተባ ግለሰብ መጣጥፍ አዘጋጅቶ በትግረይ ኦንላይን ድረ-ገጽ ላይ ማውጣቱን በመመልከቴ ይኸ ሰውየ ይህን ርዕስ የመረጠው ምን ለማለት ፈልጎ ይሆን በማለት ጽሁፉን ለማንበብ ስሞክር ተራ ውንጀላና በጥላቻ ላይ ተመስርቶ የተሰነዘረ ትችት (ስድብ ማለት ይቀላል) ሆኖ አገኘሁት፡፡ ሆኖም የዚህ አይነቱን መረን የለቀቀና አንዱን ወገን ተገን አድርጎ ሌላኛውን እነደዚህ ጥላሸት በመቀባት የሚያበሻቅጥና ብሎም የሚወንጅል ጽሁፍ አንበቦ ዝም ማለት በራሱ ተገቢ መስሎ ስላልታየኝ እኔ በተረዳሁበትና በማውቀው ልክ አጠር ያለ ምላሽ መስጠት እንደሚገባው በማመን ብዕሬን ከወረቀት (ኮምፒተር) ጋር በማገናኘት ቀጥሎ የተመለከተውን አስተያየት ለማቅረብ ፈለግሁ፡፡

ከርዕሱ በቀላሉ መረዳት እንደሚቻለው በአንድ አገር ወይም ድርጅት ውስጥ የስርአቱ ሰው መስሎ በመግባት ወይም በማቀንቀን ነገር ግን የስርአቱ ዋነኛ ባለቤት የሆነውን የወገን ሀይል በእጅጉ የሚያጠቃ ግለሰብ ወይም መሪ እንዳሻው እየሆነ ባለበት ሁኔታ እንዴት ስልጣን ላይ እንዲቆይ ይደረጋል የሚል ጠንከር ያለ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ መልክትን ያዘለ ሆኖ እናገኘዋለን፣ በእርግጥ ካለፈው አመት ጥር ወር ጀምሮ ውራይና መጽሄት፣ አይጋ ፎረምና ትግራይ ኦንላይን ድረ-ገጾች ላይ የትግራይ ተወላጆችና የመብቱም ተሚጋቾች ነን በሚሉ ወገኖች አማካኝነት እየተጻፉ ወይም ቃለ መጠይቅ አደረግን እያሉ የሚወጡ ጽሁፎች በአማራ ክልል መንግስት መሪዎችና በገዥው ፓርቲ ብአዴን ላይ ያነጣጠሩ ሆነው አግኝቻቸዋለሁ፡፡

አንዳንዱማ ስራየ ተብሎ የተያዘ ይመስላል፣ ለምሳሌ በቋራ ወረዳ ሽንፋ ከተማ ውስጥ በተቀሰቀሰው ግጭት ሳቢያ የበርካታ ሰዎች ንብረት የወደመ ቢሆንም የትግራይ ተወላጆች ተለይተው የተጠቁ ይመስል የተወሰኑ ግለሰቦችን አደራጅተው ወደ ክልሉ መንግስት የስራ ሀላፊዎች ከመላክ አልፈው የፌዴራል መንግስት ም/ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ የተለያዩ የስራ ሀላፊዎችን ቢሮ በር እንዲያንኳኩና የማሳጣት ስራቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ በአይጋ ፎረም ድረ-ገጽ ጋዜጠኛ ተብየ ግለሰብ አጋፊሪነት በሰፊው ተንቀሳቀሱ፡፡ በውራይና መጽሄት ላይ ደግሞ *"መጺኡ ነገር ብጎንደር"* (ነገር መጣ በጎንደር) በሚል ርዕስ መሰረተ ቢስ የሆነ ትንታኔ በማቅረብ በክልሉ አመራር ላይ የውንጀላ መአት ለማውረድ ጥረት ተደረገ፡፡

ይህ ሁኔታ አልበቃቸው ሲል ደግሞ በቅማንትና በአማራ ብሔረሰቦች መካከል ተከስቶ የነበረውን ውጥረትና የተወሰነ አለመግባባት እንደ መሳሪያ በመጠቀም ወደ ተካረረ ደረጃ እንዲደርስና አለመግባባቱ ወደ ግጭትነት አድጎ ከፍተኛ የሆነ የሰው ህይወት እንዲጠፋና ንብረት እንዲወድም በማድረግ በክልሉ ህዝብና በመሪ ድርጅቱ ብአዴን መካከል በቀላሉ ሊሽር የማይችል ጠባሳ እንዲፈጠር ጥረት አደረጉ፡፡ ይህንንም የትግራይ ተወላጅና የህወሀት አቀንቃኝ እንደሆነ በሚነገርለት ዶ/ር አዲሱ ገ/እግዚአብሔር የሚመራው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን አማካኝነት እንዲመረመርና የአማራ ክልል መንግስትን ተጠያቂ በሚያደርግ መልኩ ሪፖርትም እንዲዘጋጅበት ተደረገ፡፡

ይኸ ሁሉ ሲሆን የክልሉ መንግስት የስራ ሀላፊዎችም ሆኑ የገዥው ፓርቲ ብአዴን መሪዎች ችግሩን በቀላሉ መያዝና ብሎም ያለምንም ግጭት መፍታት ሲችሉና ሲገባቸውም ብሎም ያልተፈለገውንና ተደግሶላቸው የነበረውን ግጭትም በእንጭጩ መቅጨት ሲኖርባቸው የተወሰኑ የትምክህት ሀይሎች የሚያራግቡትንና የቅማንትን ትክክለኛ የማንነት ጥያቄ ለማዳፈን የሚጥሩትን ወገኖች ሀሳብ በመስማት ተቃራኒውን መንገድ በመምረጣቸው ከዛም አልፎ የቅማንት ህዝብ ወኪል የሆኑትንና ህጋዊ በሆነ መንገድ የህዝቡን ጥያቄ ይዘው በአደባባይና ሰላማዊ በሆነ መልኩ የሚንቀሳቀሱትን ወገኖች በማዋከብና የተወሰኑትን ደግሞ ያለ አግባብ በማሰር ጭምር ጥያቄውን ለማዳፈን ሞከሩ፡፡

የሚያሳዝነው ነገር በዚሁ ጥያቄ ላይ የክልሉ መንግስት ህግ አውጭው ም/ቤት ለሶስት ጊዜ ያህል እጅግ ሲበዛ ችግር ያለበትን ውሳኔ እንዲያስተላልፍ የተደረገውም በእነዚሁ ትምክህተኛ ወገኖች በሚቀርብ የተሳሳተ መረጃና በኮሚቴው ውስጥ ሆነው ለህወሀት ጠባብ ፍላጎት መሳካት መሳሪያ ሆነው በአካባቢው ሰላም እንዲደፈርስ ያገለግሉ በነበሩ ግለሰቦች መካከል ተወጥሮ በመገኘቱ ነው፡፡

ከዛም አልፎ ይህን አሳሳቢ ማህበረ-ፖለቲካዊ ሁኔታ የክልሉ መሪዎች በሰከነና በብስለት ተመልክተው ዘላቂ በሆነ አኳኋን መፍታት ባለመቻላቸውም የኋላ ኋላ በተከሰተው ግጭት ለዘመናት ተስማምተውና ተከባብረው ብሎም ተጋብተውና ተዛምደው በኖሩት የአማራና የቅማንት ብሔረሰብ አባላት መካከል ያልተጠበቀና ያልተፈለገ ግጭት ተከስቶ የክልሉ የጸጥታ ሀይሎችም ችግሩን በብልሀት ይዘው ከመፍታት ይልቅ በማን አለብኝነት ስሜት ውስጥ ሆነው ወደ ሀይል እርምጃ በማዘንበላቸው ሳቢያ የበርካታ የሰው ህይወት እንዲጠፋ፣ ንብርት እንዲወድምና በአካባቢው አለመረጋጋት እንዲፈጠር ምክንያት ለመሆን በቁ፡፡

በእነዚህና በሌሎችም የመልካም አስተዳደር ችግሮች መከሰት ሳቢያ የክልሉ ህዝብና መንግስት አጣብቂኝ ውስጥ ለመውደቁ አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና ተከታዮቻቸው በቀጥታ እንዲሁም መሪ ድርጅቱ ብአዴን በተዘዋሪ ተጠያቂ መሆናቸው አሌ የሚባል ጉዳይ አይደለም፡፡ ያም ሆኖ ግን አቶ ብርሀነ ካህሳይም ሆኑ ሌሎች የትግራይ ተወላጅ ነን ባይ ጸሀፊዎች እንደሚያቀርቡት ዘረኛ የሆነ ክስና ውንጀላ በአካባቢው ለተፈጠረው ምስቅልቅል አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ በተለይም በትግራይ ተወላጆች ላይ ለደረሰው ጥፋት በአቶ ገዱ የሚመራው የክልሉ አስተዳደርና ብአዴን ብቻ ሳይሆኑ ተጠያቂዎች የሚሆኑት ህወሀት/ኢህአዴግና መሪዎቹም ጭምር መሆናቸውን መዘንጋት የለበትም፡፡

ምክንያቱም ይህን በጠባብ ብሔር-ብሔረሰብ ላይ የተመሰረተና በእጅጉ ዘረኛ የሆነ አስተሳሰብ ኮትኩቶ በማሳደግ ህይወት እንዲዘራበት ያደረገው ህወሀት/ኢህአዴግ እንጂ እኔ እስከማውቀው ድረስ ኢህዴን/ብአዴን አይደለም፣ ከዛም በሻገር በቅርቡ በአደባባይ እንደተጋለጠው በርካታ የአማራ ክልል አካባቢዎችን (በዋነኛነት ሰሜን ጎንደርና ሰሜን ወሎ ውስጥ የሚገኙ ወረዳዎችን) አንድም በካርታ አሊያም በስም በመጥቀስ የትግራይ ክልል አካል እንደሆኑ አስመስሎ በማሳየት የትግራይ ታዳጊ ህጻናት የውሸት ትምህርት እንዲማሩ በማድረግ ረገድ ጥረት ያደረገውና በዚህም ምክንያት በአማራ ክልል ህዝቦች በአጠቃላይና በአማራ ወጣት ምሁራን በተለይ ላይ ከፍተኛ የሆነ ቅሬታ እንዲከሰት ሁኔታውን ያመቻቸው ህወሀት እንጂ ብአዴን አልነበረም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይም ቀደም ሲል በነበረው የድንበር አከላለልም ሆነ በማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት በመላ አገሪቱ ውስጥ የህወሀትና የትግራይ ተወለጆች የበላይነት ጎልቶ እንዲታይ በማድረግ ረገድ አበክሮ የሰራው ህወሀት/ኢህአዴግ እንጂ አጃቢው ብአዴን አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ አቶ ብርሀነ የድፍረቱ ድፍረት ይህን ሁሉ ሀቅ ወደ ጎን በመተው ለምን ተደፈርን አይነት ስሜት በተቀላቀለበት ስሜት ውስጥ ሆኖ በሚከተለው መልኩ ሀሳቡን በማቅረብ ራሱ ከሳሽና ራሱ ፈራጅ ለመሆን ይዳዳዋል፡፡ በመሆኑም እንደ አቶ ብርሀነ አባባል ከሆነ፡

Gedu Andargachew should have been dismissed from office a long time ago for complicity in the unrest that was ignited in some parts of Amhara region. To expect him to vacate his seat on his own volition as Muktar Kedir and Asther Mamo did in Oromia region, would have been too much to expect from a disreputable human being devoid of basic integrity.

ይህ አረፍተ ነገር ወደ አማርኛ ሲመለስ *“ገዱ አንዳርጋቸው በአማራ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በተከሰተው ሁከትና ብጥብጥ እጁ ያለበት በመሆኑ ቀደም ሲል ነበር ከስልጣን መባረር የነበረበት። ይህን ክብር የሌለውንና እምነት ብሎም የሞራል ብቃት የጎደለውን ግለሰብ  እንደ ኦሮምያዎቹ ሙክታር ከድርና አስቴር ማሞ በፈቃዱ ስልጣን ይለቃል ብሎ መጠበቅ እጅግ በጣም ስህተት ወይም ምኞት ነው።”* በማለት ሊሳለቅ ከመሞከሩም በላይ በዚህ ብቻ ሳይወሰን የአማራ ክልል ህዝቦችን ሁኔታ ከትግራዮች ባህሪ ጋር ለማነጻጸር ያመቸው ዘንድም ወደ እናት ክልሉ በመጓዝ የሚከተለውን ድፍረትና አጉል ትዕቢት የተሞላበትን ሀሳብ በማቅረብ የክርክሩን ተገቢነት ለማጠናከር ይሞከራል፡፡

Tigrians fought and defeated the most powerful army in black Africa and placed Ethiopia among the fastest growing economies in the world. If it was not for the Tigrians, the likes of Gedu and the stout Demeke would not have been where they are today. But what is most gratifying is that no report of retaliatory measures against any Amhara residing in Tigrai have been conveyed and this genuinely exemplifies that we Tigrians are civilized, tolerant, magnanimous and a cut above the rest.

ከላይ የተጠቀሰው ሀሳብ አሁንም ወደ አማርኛ ሲመለስ *“ትግራዮች በጥቁር አፍሪካ በጠንካራነቱ ይታወቅ የነበረውን የጦር ሀይል ታግለው በማሸነፍ ኢትዮጵያን ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ካስመዘገቡ የአለም አገሮች ተርታ እንድትሰለፍ አድርገዋል፡፡ ትግራዮች ታግለው ይህን ምቹ ሁኔታ ባይፈጥሩ ኖሮ እንደ ገዱ አይነቶቹና ግዙፍ ሰውነት ብቻ የተሸከመው ደመቀ ዛሬ የሚገኙበት የስልጣን ደረጃ ላይ ባልደረሱ ነበር፡፡ ይበልጥ የሚያስገርመው ነገር ደግሞ ትግራይ ውስጥ በሚኖሩ አማሮች*

*ላይ የአጸፋ እርምጃ መፈጸሙን የሚያመለክት ሪፖርት አለመሰማቱ ሲሆን ይህ ሁኔታ እኛ ትግራዮች በእውነትም ከሌሎች ኢትዮጵያዊያን በተሻለ ስልጡን፣ በመቻቻል የምናምን፣ ሆደ ሰፊና ትሁት መሆናችንን ያሳያል፡፡"*

በማለት ደፋሩና ትዕቢተኛው ብርሀነ ካህሳይ በዚህች አገር ሁለንተናዊ ለውጥ ላይ የራሱን ብሔር አባላት አስተዋጽኦ ከሚገባው በላይ አጉልቶ ለማሳየት ስለፈለገ የአማራ ክልል ህዝቦች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች የኢትዮጵያ ብሔሮችችና ብሔረሰቦችም ጭምር ያን ያህል ያልሰለጠኑ፣ በመቻቻል የማያምኑ፣ እጅግ ጠባብና ለራሳቸው ነጻነትም ሆነ ለሀገራቸው ፈጣን ምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት መመዝገብ ርባና ያለው አስተዋጽኦ ያላበረከቱ መሆናቸውን በተዘዋዋሪ መልኩ በድፍረት ለመግለጽ ሞከረ፡፡ ይህን ድፍረት የተሞላበት መጣጥፍ አስመልክቶ ተኮላ መኮንን የተባለ ጸሀፊ

"ይህን (መጣጥፍ) ሳነብ ፈራሁ፣ ጽሁፉን አንብቤ መጨረስም ከበደኝ። የአእላፍ የኢትዮጵያ ልጆች በትግል የፈሰሰ ደም ደመ ከልብ ነው ሲባል ስሰማ፡ ትግሬ ነጻ ባያወጣችሁ ኖሮ የሚል ትምክህት ሳነብ ጸሐፊው ሊያበጣብጡ የተነሱ 5ኛ እረድፈኛ እራሳቸው መሆናቸው ተገለጠልኝ። ማንም ኢትዮጵያዊ የበታች ሆኖ የተወሰኑ የሚኩራሩባት፣ ቀሪዎች የሚሰደቡባት ኢትዮጵያ እንደማትኖር ለወንድሜ ልነግራቸው ተነሳሁ። በሳቸው ብእር የትግራይን ሕዝብ መገምገም አልፈልግምና፣ የትግራይን ሕዝብ እኔም እንደሳቸው አውቀዋለሁና፣ ለሕዝቡ ያለኝን ፍቅርና አክብሮት በሳቸው ተራ አመለካከት እንደማላጨልመው በመንገር ጽሑፉ የእሳቸውን የከሰረ የግለሰብ አመለካከት የሚያሳይ ተራና እንጭጭ መሆኑን ሳልነግራቸው ማለፍ ግን አልፈለግሁም።"

በማለት በዚሁ ኦንላይን ላይ ለአቶ ብርሀነ ካህሳይ መልስ በሰጡበት ጽሁፋቸው አማካኝነት ሀሳባቸውን ለመግለጽ እንደተገደዱ ተመልክቻለሁ፡፡ በዚህ አጋጣሚ በአቶ ተኮላ ሀሳብ እኔም ሙሉ ለሙሉ እንደምስማማ ለመግለጽ አወዳለሁ፣ መሾሙንም ሆነ መሻሩን እንዲሁም የወንጀል ድርጊት ፈጽመውም ከሆነ የመከሰሳቸውን ሁኔታ ለአማራ ክልል ህዝቦችና እነሱን ለሚወክላቸው ለክልሉ ም/ቤት ቢተወው መልካም ነበር፡፡ በአጠቃላይም እኛ ትግራዮች በማለት ይህን ጨዋና ሰው አክባሪ ህዝብ መነገጃ ባያደርገውም ጥሩ ነው፡፡

ታዲያ ምን ያደርጋል አቶ ብርሀነ የራሱን ሀሳብ በሌሎች ላይ መጫኑን እንጂ እንደ ትልቅ ቁም ነገር አድርጎ የወሰደው ሌሎች ምን ሊሰማቸውና ምን አይነት ምላሽስ ሊሰጡ ይችላሉ የሚለውን ሀሳብ ለማገናዘብ አይፈልግም፣ ከዛም አልፎ ደፋሩና ትቢተኛው ጸሀፊ አቶ ገዱ አንዳርጋቸውን በተመለከተ የሚከተሉትን ነጥቦች በማንሳት እስካሁን ድረስ እንዴት ስልጣን ላይ ሊቆዩ እንደቻሉ ይጠይቃል፤ገዱ አንዳርጋቸው እኮ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተጠያቂ ነው በማለት ጭምር መረጃ አልባ የሆነውንና በጥላቻ ስሜት ብቻ የሚነዳ የውንጀላ ሀሳቡን ለማጠናከር ይሞክራል፡-

- ለግብጽና ለተላላኪያቸው የኤርትራ መንግስት የጥፋት ድርጊቶች በር በመክፈቱ፣
- በውጭ ባለሀብቶችና ኢንቨስተሮች ሀብትና ንብረት ላይ ጉዳት እንዲደርስ በማድረጉ፣
- በትግራይ ብሔር አባላት ላይ የጥላቻ ቅስቀሳ በማድረግና በጥረታቸው ለፍተው ያፈሩትን ሀብትም በማዘረፉ፣
- በውጭው አለም የኢትዮጵያ ገጽታ እንዲበላሽ በማድረጉ፣
- ወደ ሌላው የሀገሪቱ አካበቢ ሁከትና ብጥብጥ እንዲዛመት በማድረጉ፣
- የቅማንት ብሔረሰብን ራስን በራስ የማስተዳደር ህገ-መንግስታዊ መብት በመንፈጉ፣
- የወልቃይትን ኮሚቴ ጎንደር ላይ በማደራጀት የትግራይን ክልል መንግስት እንዲገዳደር በማድረጉ፣
- ወልቃይት የሚኖሩ የትግራይ ብሔር አባላትን ማንነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ በማድረጉና በትግራዮች ላይ በጥላቻ ላይ የተመሰረተ የቅስቀሳ ዘመቻ በመክፈቱ፣
- በብአዴን፣ በፖሊስና በጸጥታ ሀይሉ እንዲሁም እስከ ቀበሌ ድረስ በሚገኘው የክልሉ መንግስት መዋቅር ውስጥ የአሸባሪው ግንቦት-7 ሰርጎ እንዲገባ በማድረጉ፣
- በኢትየጵያ ባለፉት 25 አመታት የተሰራውን የሰላምና ማረጋጋት ስራ ጥያቄ ውስጥ እንዲወቅ በማድረጉ፣
- የውጭ ባለሀብቶችን ንብረት መጠበቅ ባለመቻሉ ምክንያት በክልሉ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የስራ አጥነተ እንዲስፋፋ በማድረጉ ወዘተ.

ከያዘው ስልጣን መውረድ ብቻ ሳይሆን በወንጀል ተከሶ እስር ቤት መግባት እንደነበረበትም ሀሳቡን ያቀርባል፣ የዚህ አይነቱ መረን የለቀቀ ብቸ ሳይሆን ወጥ የረገጠና ቀይ መስመር የተላለፈ የእኔ አውቅልሀ አለሁ ሀሳብና አስተያየት ብሎም እሱን መሰል አዛኝ ቅቤ አንጓቾች አማካኝነት ከአንዳንድ የትግራይ ተወላጆች ነን ከሚሉ ወገኖች በድፍረት ተጽፎ መቅረቡ ብዙም አዲስ ነገር ላይሆን ይችላል፡፡ የዚህኛው ግን ሀይ ባይ ጠፍቶ ነው እንጂ በእጅጉ ቀይ መስመር ያለፈ ብቻ ሳይሆን ይልቁንም

በትግራይ ብሔር አባላት ስም የሚነግድ የህወሀትም ይሁን የትግራይ ህዝብ ጠላት እንጂ ወዳጅም ሆነ ተቆርቋሪ ሊሆን የሚችል ሰው አይደለም፡፡

ሙሉ የጽሁፉን ይዘት ቃል በቃል ተርጉመን ለመላው የብአዴን አባላትና ለአማራ ክልል ህዝቦች ብናቀርበው በትግራይ ተወላጆች ላይ ሊፈጥረው የሚችለውን አሉታዊ ስሜት ማንም ሰው አስቀድሞ መገመት የሚችል ይመስለኛል፡፡ ሆኖም እኛ እሱንና መሰሎቹን አይደለንምና እንደሱም ያን ያህል ለመውረድ የሚያስችል የሞራልም ሆነ የስነ ምግባር ዝቅጠት ደረጃ ላይ ባለመድረሳችንም ጭምር የተወሰነውን ብቻ ለአብነት በመጥቀስ የዚህ አይነቱ ወጥ የረገጠ ሀሳብ ሲመጣ ድረ-ገጹም ሆነ አዘጋጆቹ እንዳለ ለማስተናገድ ባይሞክሩ መልካም ነው የሚል መልዕክትም በማስተላለፍ መጠቆም ተገቢ ይመስለኛል፡፡

ካልሆነ ግን በእርግጥም ድረ-ገጹ ራሱና አዘጋጆቹ ለዚህ አይነቶቹ የጥፋት መልዕክተኞች መፈንጪያ ይሆኑና ኋላ ላይ በቀላሉ ሊስተካከል የማይችል ጠባሳ ሊያሳርፍ የመቻል ዕድሉ ሰፊ ይሆናል፡፡ በዚህ ሁኔታ ደግሞ የትግራይ ህዝብም ሆነ ህወሀት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ሁኔታ አይኖርም ብቻ ሳይሆን የዚህ አይነቱ ዘረኛ ቅስቀሳና የአጉል መታበይ ሀሳብ ሰለባ የሚሆኑበት አጋጣሚ መፈጠሩ አይቀሬ ነው፣ በትንሹም ቢሆን በሰሜን ጎንደርና አካባቢው ከተከሰተው ሁከትና ብጥብጥ መማርም ብልህነት ይመስለኛል፡፡ በሌላ አገላለጽ ህወሀትና የትግራይ ህዝብ ሊጠቀም የሚችለው ገንቢ የሆነ ሂስ በብአዴንም ሆነ በአማራና በትግራይ ክልል መንግስታት መሪዎችና በህወሀት አመራር ላይም ጭምር ቅን ሂስ መሰንዘር ሲቻልና ሚዛነዊ በሆነ አቀራረብ ለማስተማር ጥረት ሲደረግ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

ቸር ይግጠመን!